

በፕሬዘደንት ሔንሪ ቢ. አይሪንግ
የቀዳሚ አመራር የመጀመሪያ አማካሪ

እውነተኛ ደቀ መዝሙራን መሆን

በእያንዳንዱ የቅዱስ ቁርባን ስብሰባ ላይ፣ ሁልጊዜ አዳኝን እንደምናስታውስ እና የሱም መንፈስ ከኛ ጋር እንዲሆን ትእዛዛቱን ለመጠበቅ ቃል የመግባት እድሉ አለን። (ሞሮኒ 4፥3፤ 5፥2፤ ት. እና ቃ. 20፥77፣ 79ተመልከቱ)። የሱን ስም በላያችን ላይ ስንወስድ እርሱን ማስታወስ ሁልጊዜ በተፈጥሮ ወደ እኛ ይመጣል። በብዙ መንገዶች ይህንን እናደርጋለን ነገር ግን በተለይ ደግሞ የምናደርገው በስሙ ሌሎችን ስናገለግል፣ ቅዱስ ቃላቱን ስናነብ፣ እና እርሱ እኛ ምን እንድናደርግ እንደሚሻ ለማወቅ ስንጸልይ ነው።

ለእኔ የተከሰተው ለአንድ ወጣት ጥምቀትን በማደርግበት ወቅት ነበር። በአዳኝ በተሾሙ አገልጋዮች የሚሰዮን አገልጋይ እንድሆን እና ወንጌሉን እንዳስተምር እናም ስለ እርሱ እና ስለ እውነተኛው ቤተክርስቲያን እንድመሰክር እንደተጠራሁ አወኩኝ። የአገልግሎት አጋሪዬ እና እኔ ለወጣቱ ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ የሃጢያት ክፍያ ሃይል ምክንያት ንስሃ በአዳኝ ላይ ባለው እምነት ከገባ እና ስልጣን በተሰጣቸው አገልጋዮች ከተጠመቀ እንደሚነጻ ቃል ገባንለት።

ወጣቱን ከጥምቀት የገንዳ ውሃ ውስጥ ከፍ ሳደርገው በጆሮዬ ላይ "ንጹህ ነኝ፣ ንጹህ ነኝ" በማለት አንሾካሾከ። በዛ ቅጽበት፣ በዮርዳኖስ ወንዝ በመጥምቁ ዮሃንስ የተደረገውን የአዳኝን ጥምቀት አስታወስኩኝ። በተጨማሪም እንኳ፣ ትንሳኤ ባደረገውና በህይወት ያለውን የአዳኝን የማዳን ስራ ለዮሃንስ እንደሆነው በመንፈስ ቅዱስ ታጅቤ እየሰራሁ እንደሆነ አስታወስኩኝ።

ለእኔና ለእያንዳንድችን፣ አዳኝን ማስታወስ ካሉን የትውስታ እውቀት እና ከእርሱ ጋር ባሉን ተሞክሮዎች ከመመርኮዝ ይልቅ የበለጠ ሊሆን ይችላል። ይበልጥ ወደ እሱ በአሁኑ ወቅት እንድንቀርብ የሚያደርጉ ምርጫዎችን በየቀኑ ማድረግ እንችላለን።

ቀላሉ ምርጫ ቅዱሳት መጻህፍትን ማንበብ ሊሆን ይችላል። እንዲህ በማድረግ፣ ለእርሱ ቅርብ የመሆንን ስሜት ማግኘት እንችላለን። ለእኔ፣ መፅሐፈ ሞርሞንን በማነብበት ጊዜ ቅርብ የመሆን ስሜት አብዛኛውን ጊዜ ወደ እኔ ይመጣል። በሁለተኛ ኔፊ ካሉት ምዕራፎች ውስጥ በማነብበት በመጀመሪያ ደቂቅዎች ውስጥ፣ የኔፊንና የሌሂን ድምጾች በአይምሮዬ ውስጥ አዳኝን በግል እንደሚያውቁት ሲገልጹ ይሰማኛል። የቅርበት ስሜት ይመጣል።

ለእናንተ፣ ሌሎች የቅዱስ መጽሃፍት ቃሎች በተለይ ወደእርሱ ሊያቀርባችሁ ይችላል። ነገር ግን የትም ቢሆን መቼም የእግዚአብሄርን ቃላት በምታነቡበት ወቅት፣ በትህትና እና በቀና አመለካከት አዳኝን ስትመለከቱ፣ በለት ተለት ህይወታችሁ የእርሱን ስም በላያችሁ ለመውሰድ ያላችሁን መሻት ትጨምራላችሁ።

ያም መሻት በጌታ ቤተክርስቲያን ውስጥ የምትሰጡትን የአገልግሎት መንገድ ይቀይራል። ለእናንተ ትንሽ ጥሪ መስሎ የሚታየውን እንኳ እንዲያነሳው እርዳታ ለማግኘት የሰማይ አብን ተለምናላችሁ። የምትጠይቁትም እርዳታ ራስህን የመርሳት እና አዳኝ እናንተ እንድታገለግሏቸው ለተጠራችሁባቸው ሰዎች፣ ለእነርሱ የሚፈልገው ነገር ላይ ይበልጥ ትኩረት ለማድረግ ነው።

በልጆቻችን አገልግሎት ውስጥ ወንጌል ብቻ የሚያመጣውን ሰላም እነሱ እንዲያገኙ እንዴት ለመርዳት ማወቅ እንድችል በጸለይኩበት ጊዜ የእርሱ እጅ እና ቅርበት ተሰምቶኛል። በእነዚህ ጊዜያት፣ ውጤታማ ወላጅ ሆኖ መታየቱ ግድ አላለኝም፣ ነገር ግን ስለልጆቼ ውጤታማነትና ደህና መሆን በጥልቀት ግድ አለኝ።

አዳኝ ሊሰጣቸው የሚችለውን ነገሮች ለምናገለግላቸው ሰዎች የመስጠት ፍላጎት ወደሰማያዊው አባታችን *የተማጽኖ፣ በእውነቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም* እንድንጸልይ ያደርገናል። በዚህ መልኩ ስንጸልይ—በአዳኝ ስም፣ በእርሱ ላይ እምነትን በማድረግ—አብ ይመልሳል። እሱም መመሪያ፣ መጽናናትን፣ እና እኛን ለማበረታታት መንፈስ ቅዱስን ይልካል። መንፈስ ሁልጊዜ ስለ አዳኝ ስለሚመሰክር

(3 ኔፊ 11፥32፣ 36፤ 28፥11፤ ኤተር 12፥41ተመልከቱ)፣ ጌታን በሙሉ ልባችን፣ አእምሮ፣ እና ጥንካሬ የማፍቀር ያለን አቅም እየጨመረ ይሄዳል (ማርቆስ 12፥30፤ ሉቃስ 10፥27፤ ት. እና ቃ. 59፥5 ተመልከቱ)።

በየቀኑ እና በየጊዜው የማስታወስ በረከት በዝግታ እና ያለማቋረጥ በምናገለግለው ጊዜ፣ ቃሉን ስንመገብ እናም በስሙ በእምነት ስንጸልይ ይመጣል። እናም ይህም ማስታወስ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ባለው መንግስቱ እና በኋላ ደግሞ በሚመጣው በክብር በተሞላው አለም እውነተኛ ደቀመዝሙር እንድንሆን ያዘጋጀናል።

ከዚህ መልእክት ማስተማር

ፕሬዘደንት አይሪንንግ ወደ አዳኝ ቅርብ ለመሆን የሚያስቸሉ የለት ተለይ ምርጫዎችን ለማድረግ እንድናስታወስ አበረታትተውናል። ከምታስተምሯቸው ጋር፣ እሱን ሁልጊዜ እንድናስትውስ የሚገባበትን ቃል ኪዳን የሚዘረዝረውን የቁርባን ጸሎት ማንበብ ትችላላችሁ (ሞሮኒ 4፥3፤ 5፥2፤ ት. እና ቃ. 20፥77፣ 79ተመልከቱ) ።እያንዳንዱ ቀን አዳኝን ለማስታወስ ማድረግ የሚችሉትን ነገሮች ዝርዝር እንዲጽፉ የምታስተምሯቸውን ሰዎች ለመጋበዝ አስቡበት። እንዲሁም አንዳቸው የሌላውን ስኬት እና ደህንነት ወደ ሰማይ አባት እንዲፀልዩ ለመጋበዝ አስቡበት። በተመሳሳይ መልኩ ለእነርሱ ለመጸለይ አስቡበት።

ወጣቶች

ጌታን ሁልቀን ማስታወስ

ጓደኞች፣ የቤት ስራዎች ሃላፊነት፣ የትምህርት ቤት ስራዎች፣ ቲቪ—ብዙ ነገሮች የኛን ትኩረት ይጠይቃሉ። ነገር ግን በየሳምንቱ፣ የሰማይ አባትን "[የሱን ልጅ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ] ሁልጊዜ እንደምናስታውስ" ቃል እንገባለታለን (ት እና ቃ 20፥79)።

ፕሬዘደንት አይሪንግ ወደ አዳኝን እንድናስታውስ የሚረዱንን የለት ተለት ምርጫዎችን መምረጥ እንደምንችል ተናገሩ። በእያንዳንዱ ቀን አዳኝን አብዝታችሁ ለማስታወስ በዚህ ወር ግብ ለማድረግ አስቡበት። ከእርሱ ጋር ያላችሁን ዝምድና ለመገንባት ካሌንደር አዘጋጁ እናም በቀን አንድ ነገር ለማድረግ ወስኑ። ፕሬዚዳንት አይሪንግ ቅዱሳት መጽሃፍትን ማንበብ፣ በእምነት መጸለይ እና አዳኝን እና ሌሎችን ማገልገል እንደምንችል ዘርዝረዋል። ደግሞም የለት ተለት ሁኔታን በማስታወሻ መመዝገብ፣ የቤተክርስቲያን ስብሰባዎች ላይ መገኘት፣ የጠቅላይ ጉባዔ ንግግሮችን ማዳመጥ፣ ቤተመቅደስ መሄድ፣ መዝሙሮችን መዘመር አሉ—ዝርዝሩም ይቀጥላል። በየለቱ ጌታን ስናስታውስ፣ ፕሬዝዳንት አይሪንግ " በረከቶቹ በዝግታ እና ያለማቋረጥ እንደሚመጡ እና የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዝሙር እንድንሆን እንደሚያዘጋጀን" ቃል ገብተዋል።

ልጆች

የፍቅር ሙላት

ቅዱሳት መጽሃፍትን ስናነብ ወይም ስንጸልይ፣ የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ምን ያህል እንደሚያፈቅሩን ይሰማናል። ተለቅ ያለ ልብ ውስጥ አንዳንድ አነስተኛ ልቦችን ሳሉ። በምትጸልዩበት ወይም ጥቅሶችን በምታነቡበት በእያንዳንዱ ጊዜ በአንድ ልብ ውስጥ በቀለም አቅልሙ። ወደ ሰማይ አባታችን እና ወደ ኢየሱስ ቅርበት እንዲሰማን ምን ማድረግ እንችላለን?

© 2017 በ Intellectual Reserve, Inc. መብቶች ሁሉ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ. ውስጥ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፥ 6/16 (እ.አ.አ)። ትርጉም የተፈቀደበት፥ 6/16 (እ.አ.አ)።
First Presidency Message, October 2017 ትርጉም። Amharic 97930 506

ከመሰመር የወጡትን በፍቅር ማቀፍ

በጸሎት መንፈስ ይህንን መረጃ አንብቡት እና ምን እንደምታካፍሉ ለማወቅ የመንፈስ ምሪትን እሹ። የሴቶች መረዳጃ ማህበር እቅድን ማወቅ እንዴት የእግዚአብሔር ሴት ልጆችን ለዘለአለማዊ ህይወት በረከቶች ያዘጋጃል?

እምነት ቤተሰብ እርዳታ

የቀዳሚ አመራር ሁለተኛ አማካሪ ፕሬዘደንት ዲየተር ኤፍ. ኡክዶርፍ እንዳሉት፣ “እውነታው ምንም ፍጹም ቤተሰቦች የሉም . . . ፣”። “ቤተሰባችሁ የትኛውም አይነት ችግሮች ቢጋፈጡም፣ ችግሩን ለመፍታት ምንም አይነት ነገር ብታደርጉም፣ የመፍትሄው መጀመሪያ እና መጨረሻ የክርስቶስ ንፁህ ፍቅር የሆነው ልግስና ነው።”[1]

ወንጌልን በሙሉነት ለማይከታተሉ፣ ሊንዳ ኬ. በርተን፣ የቀድሞ የጠቅላይ የሴቶች መረዳጃ ማህበር ፕሬዝዳንት የነበሩት እንዳሉት፣ “የሰማይ አባት ሁሉንም ልጆቹን ይወዳል። . . . የትም ቢሆኑ—በመንገዱም ሆነ ከመንገዱ ውጪ ያሉ—ወደቤት እንዲመለሱ ይወዳል።”[2]

“ሆኖም ግን ምንም ያህል [ልጆቻችሁ] ዓመጸኛ ቢሆኑም፣ . . . ስታናግሯቸው፣ በንዴት ውስጥ አታድርጉት፣ በመንቀፍም አታድርጉት፣ በመኮነን መንፈስ አታድርጉት፣” ብለው ፕሬዝዳንት ጆሴፍ ኤፍ. ስሚዝ (1838-1918 እ.አ.አ) አስተማሩ። “በቀናነት አናግሯቸው።”[3]

ሽማግሌ ብረንት ኤች. ኔልሰን የሰባ ጉባኤ አባል አስር ድሪም ላላቸው እና አንዱ ለጠፋባቸው፣ “እስከምታገኙት ድረስ ፈልጉት” ያለውን የአዳኝን ምሪት ደግመው ተናግረዋል። የጠፋው የወንድ ወይም የሴት ልጃችሁ፣ ወንድማችሁ ወይም እህታችሁ ስትሆን፣ . . . ለምድረግ ከምንችለው ነገሮች ሁሉ በጓላ፣ ያንን ሰው በሙሉ ልባችን እንወደዋለን። . . .

“እናንተ እና እኔ ሌሎችን በሕይወታችን ውስጥ የጠፉትን ሰዎች እንዴት እንደምንቀርብ ለማወቅ እናም፣ አስፈላጊ ሲሆንም፣ አባካኙን ለማፍቀር፣ ለመመልከት እና ለመጠበቅ የሰማይ አባታችን እና የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ተዕማስት እና ፍቅር እንዲኖረን ራዕይ እንቀበል።”[4]

ፕሬዘደንት ሔንሪ ቢ. አይሪንግ፣ የቀዳሚ አመራር የመጀመሪያ አማካሪ፣ እንዳሉት፣ “የምወደው ሰው የቤዛነቱን ሃይል እንዲፈልጉና እንዲሰማቸው በእምነት ጸልያለሁ። የሰው መላእክትም ለእርዳታ ወደነርሱ እንዲመጡ ጸልያለሁ፣ እናም መጥተዋል።

“እግዚአብሄር እያንዳንዱ ልጆቹን ለማዳን መንገድ አዘጋጅቷል።”[5]

ተጨማሪ የቅዱሳት መጻህፍት ጥቅሶች እና መረጃ

ማቴዎስ 18፣ 12፤ አልማ 31፣ 35፤ 3 ኔፊ 13፣ 32፤ ት. እና ቃ. 121፣ 41–42

reliefsociety.lds.org

ማስታወሻዎች

1. ዲየትር ኤፍ. ኡክዶርፍ፣ “In Praise of Those Who Save,” *Liahona*, ግንቦት 2016 (እ.አ.አ)፣ 79፤ 80።
2. ሊንዳ ኬ. በርተን፣ በሳራህ ጂን ዊሽር፣ “Sister Burton, Sister Wixom Visit Church’s Pacific Area፣” ውስጥ *Church News* ሚያዝያ 2፣ 2013 (እ.አ.አ)፣ lds.org/church/news{64}።
3. *Teachings of Presidents of the Church: Joseph F. Smith* (1998), 254።
4. ብረንት ኤች. ኔልሰን፣ “Waiting for the Prodigal፣” *Liahona*፣ ግንቦት 2015 (እ.አ.አ)፣ 103።
5. ሔንሪ ቢ. አይሪንግ፣ “To My Grandchildren፣” *Liahona*፣ ህዳር. 2013 (እ.አ.አ)፣ 71።

ይህን አስቡበት

የወንጌልን መርሃ ግብሮች ለማይኖሩ ሰዎች እንዴት አድርገን ቀጣይ የሆነ ልግስና ማሳየት እንችላለን?

© 2017 በ Intellectual Reserve, Inc. መብቶች ሁሉ የተጠበቁ። በዩ.ኤስ.ኤ. ውስጥ የታተመ። እንግሊዘኛ የተፈቀደበት፣ 6/16 (እ.አ.አ)። ትርጉም የተፈቀደበት፣ 6/16 (እ.አ.አ)።
Visiting Teaching Message, October 2017 ትርጉም። Amharic 97930 506